መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
አቅራቢዎች

# ሕዝቅኤል ፤ የራዕይ ሰው።



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Lazarus, Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2022 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ከብዙ አመታት በፊት ፣ ኃያል የሆነ ሰራዊት ብዙ የእግዚአብሔር ሕዝብን ወደ ይሁዳ ለምርኮ በምርኮ በመውሰድ ይሁዳን አጠቃ። ከሐገራቸው ርቀው ፣ ኮቦር በሚባል ወንዝ አጠገብ ኖሩ። ከእነርሱ መካከል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበረ፤ ነብዩ ሕዝቅኤል የሚባል።



አንድ ቀን ፣ እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል ራዕይን ሰጠው። የእግዚአብሔር ክብር እንደሚያበራ ፀዳል ፍም በሚመስሉ ሕያዋን ፍጥረታት ተገለጠ። እያንዳንዱም አራት ፊትና አራት ክንፍ ነበራቸው። ከእነርሱም በላይ እጅግ የተዋበና እንደ እሳት ነበልባል የሚቀጣጠል ቀስተደመና ያለበት የሰንፔር ዙፋን ነበረ ። ሕዝቅኤል ሲመለከተው ፣ በፊቱ ተደፋ።



እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል እንዲህ አለው ፤ "አንተን ወደ እስራኤል ልጆች እልክሃለሁ ፤ ቃሌን ንገራቸው። አመጸኛ ናቸውና።" እግዚአብሔርም አለው ፤" ሒድ ፤ ለእስራኤል ሕዝብ ተናገር።" እንዴት ያለ እንግዳ የሆነ ትዕዛዝ ነው!

ነገረ ግን ሕዝቅኤል ታዘዘ ፤ ጥቅልሉንም በላውና ሔደ።



የእግዚአብሔርም መንፈስ ሕዝቅኤልን
አንስቶት በኮቦር ወንዝ ዳር ወዳሉት
አይሁዳዊ ምርኮኞች
ወሰደው፡፡ ለሰባት ቀናትም
እነርሱ በተቀመጠበት ስፍራ
ተቀመጠና ባየው ነገር ሁሉ
ተደነቀ፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር
ሕዝቅኤልን ጠባቂ አደረገው፡፡
እርሱም እግዚአብሔርን የማይታዘዙ
የሆኑ ክፉ ሰዎችን ይገስጽ ነበረ፡፡





ሕዝቅኤልም የእግዚአብሔር ቃል ግለጽ ለማድረግ ብዙ እንግዳ ነገሮችን ያደርግ ነበረ፡፡ የእየሩሳሌምን ምስል በሸክላ ስባሪ ላይ ይስል ነበረ፡፡ ምንአልባት በኢየሩሳሌም ዙሪያ ያሉትን ታላላቅ ሰራዊትን በሚስልበት ጊዜ ሰዎች በትከሻው በኩል ይመለከቱ ነበረ፡፡ እርሱ የእግዚአብሔር ቅድስት ከተማ በቅርቡ እንደምትፈርስ ያሳይ ነበረ፡፡

የሰሜኑ ግዛት የሆነው እስራኤል ለሶስት መቶ ዘጠና አመታት እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ኖረዋል። ይሑዳም የደቡቡ እንዲሁ ለአርባ አመታት። በዚያም ምክንያት እስራኤል የፈረሰችውና ይሁዳም በፍጥነት የወደቀችው። እግዚአብሔርም ሕዝቅኤልን ፣ ሕዝቡ በኃጢያት የቆየበትን ዘመን ያሳስበው ዘንድ፣ ለሶስት መቶ ዘጠና ቀናት በቀኙ በኩል  እንዲሁም በግራው ደግሞ ለአርባ አመታት እንዲወድቅ ነገረው።





ምንአልባት ሕዝቡ ሕዝቅኤል እጅግ እንግዳ ሰው እንደሆነ ማሰብ ሳይጀምሩ አይቀርም፡፡ እግዚአብሔር የነገረውን ሁሉን ነገር አደረገ፡፡ አንድ ቀን ፣ ጸጉሩን ላጨውና አንድ ሶስተኛ የሚሆነውን አቃጠለው፡፡ ይሄም ፣ የባቢሎን ሰራዊት ከተማይቱን ሲያጠቃ ፣ በኢየሩሳሌም ያለ አንድ ሶስተኛው በበሽታ እና በረሃብ እንደሚሞት ለማሳየት ነበረ፡፡



ሕዝቅኤልም ሌላ አንድ ሶስተኛ የሚሆነውን የጸጉሩን ክፍል ወሰደውና በሰይፍ ቆረጠው። ይሄ ደግሞ አንድ ሶስተኛው ሕዝብ በጠላት ሰይፍ እንደሚሞት ለማሳየት ነበረ። የመጨረሻው ሶስተኛ ፣ በንፋስ ተወሰደ። ነገር ግን ጥቂት ጸጉሮችን በልብሱ ጫፍ ሰበሰበ ፤ ይሄም እግዚአብሔር ከሕዝቡ መካከል ጥቂቱን በሰላም አቆይቶ ወደ ተስፋይቶ ምድር እንደሚመልሳቸው የሚያሳይ ነው።



ይሄ ጀግና ነብይ ተማርከው ለነበሩ አይሁዳዊያን ፣
ነገሮች እየከፉ እንደሚሄዱ እንጂ እነርሱ ተስፋ
እንዳደረጉት እንደማይሆን ነገራቸው፡፡ ህዝቡም
በሕዝቅኤል ላይ ተቆጣ ፤ ነገር ግን
እርሱ የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ
ይናገር ነበረ፡፡ አንድ ቀን ፣
ከእስራኤል ሽማግሌዎችጋ ቁጭ
ባለበት ፣ እግዚአብሔር
ለሕዝቅኤል ራዕይን አሳየው፡፡
በራዕዩም ፣ አግዚአብሔር
ጸጉሩን ይዞ ወደ እየሩሳሌም
መቅደስ አስገባው፡፡



እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል፣ በመቅደሱ ውስጥ የሚሳቡና ንጹህ ያልሆኑ እንስሳትን እና ጣኦታትን አሳየው:: እኒህ ነገሮች በመቅደሱ ውስጥ መታየት ያለባቸው አልነበሩም::



መሪዎቹ በእግዚአብሔር ስፍራ እነዚህን ነገሮች ያመልኩ ነበረ፡፡ እግዚአብሔርም ክብሩ ቤተመቅደሱን እንደለቀቀና ቤተመቅደሱም እንደሚፈርስ ለሕዝቅኤል አሳየው፡፡ ራዕዩ ሲያልቅ ፣ ሕዝቅኤል ስለ ራዕዩ ለአይሁዳዊያን ነገራቸው፡፡





እግዚአብሔር ያለው ሁሉ ሆነ፡፡ ኢየሩሳሌም ፈራረሰች፡፡ ብዙ ሰዎችም ጠፉ፡፡ በምርኮ ያሉ አይሁዳዊያን ይሔንን ሲሰሙ ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለዘላለም ያጠፉ ይሆን ብለው አደነቁ፡፡



ነገር ግን እግዚአብሔር ሌላ መልእክትን ለነብዩ ነገረው፡፡ የሰው ደረቅ አጥንቶች ብቻ በሞሉበት ሸለቆ ሕዝቅኤልን መራው፡፡

እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን አለው ፤ “የሰው ልጅ ፤ እነዚህ አጥንቶች ሕያው ናቸውን ; ” ሕዝቅኤልም እንዲህ አለ ፤ “አ! እግዚአብሔር አምላክ! አንተ ታውቃለህ፡፡” እርግጥ ነው የደረቁ አጥንቶች እንደገና መኖር አይችሉም፡፡

እግዚአብሔርም አለው ፤ “በእነዚህ አጥንቶች ላይ ትንቢትን ተናገር ፤ እናም በል አ! እናንተ አጥንቶች ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፡፡”

ሕዝቅኤልም ይሄንን ሲል ፤ የሚንኳኳን ድምጽ ሰማ፡፡

ይሄንን ምን ፈጥሮታል ብለህ ታስባለህ?



ነቢዩም በአድናቆት ሲመለከት፣ አካላቱ
አጥንት በአጥንት እየሆነ መጋጠም ጀመረ፡፡



ከዚያም ፣ ስጋ ተከትሎ መጣ፡፡



ከዚያም ቆዳም ሸፈነው ፤ ነገር ግን ትንፋሽ በዚያ አልነበረም።



እግዚአብሔርም እንዲህ አለ ፣ “ተንብይ ፣ የሰው ልጅ እንዲህ በል ፣ አንተ ንፋስ ከሁሉም አቅጣጫ ና! በእነዚህም ላይ ንፈስ።” ሕዝቅኤልም ይሔንን ሲያደርግ ፣ ንፋስ ወደ እነርሱ መጣ ፤ ሕያዋንም ሆኑ፤ በእግሮቻቸውም ቆሙ። ታላቅ ሰራዊት ሸለቆውን ሞላው።



ኢየሩሳሌም ሲወድቅ ፣ በባቢሎን ያሉ አይሁዳዊያን ተስፋ ቢስ እንደሚሆኑ እግዚአብሔር ያውቅ ነበረ። በሕዝቅኤል ራዕይ ውስጥ መልዕክትን ላከ ። “እነዚህ አጥንቶች የእስራኤልን ቤት ይወክላሉ።” እግዚአብሔርም አለ ፣ “መንፈሴን በእናንተ ላይ አደርግና ወደ ሃገራችሁ እመልሳችኋለሁ።”



እንዴት ያለ ከእግዚአብሔር የሆነ ታላቅ የተስፋ መልዕክት ነው! አይሁዳዊያን ወደ ስፍራቸው ሲመለሱ ፤ እግዚአብሔር በነብዩ ሕዝቅኤል በኩል የተናገረው ሁሉ ልክ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ እግዚአብሔር ወደ ሐገራቸው እንደሚመልሳቸው ያውቁ ነበረ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ሁልጊዜም ትክክል ነው፡፡



ሕዝቅኤል ፣ የራዕይ ሰው።

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ሕዝቅኤል።

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝነት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16